# <u>ኢህአፓና አብዮታዊዉ ትዉልድ በአዳም ረታ ልብ ወለድ መጽሃፍት እይታ</u>

*ሰለሞን ገ/ስላሴ*

**አዳም ረታ የተዋጣለት የዘመናችን የልብ ወለድና የአጫጭር ታሪኮች ዝነኛ ጸሃፊ ነዉ። ከታወቀባቸዉ ዋና ዋና የልብ ወለድ ስራዎቹ መካከል፤ ማህሌት፤ ግራጫ ቃጭሎች፤ አለንጋና ምስር፤ እቴ እሜቴ የሎሚ ሽታና አሁን ደግሞ ዳጎስ ያለዉ ልብ ወለድ ስራዉ "መረቅ" ይገኙበታል።**
**በልብ ወለድ ስራዎቹ አዳም ከማንኛዉም ጉዳይ በበለጠ ሊባል በሚችል ግምት የወንድና የሴትን ዘመናዊ ግንኙነት በባልና ሚስትም መልክ፤ በዉሽማም መልክ፤ በፍቅረኛም መልክ ሰፊ ቦታ ሰጥቶ ባማረ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን፤በከፊል ወግ አጥባቂ ለሆነ ህብረተሰብ አይን ገላጭ በሆነ መልክ ያስነብባል። የወንድንና የሴትን አካላት፤ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ከወሲብ ጋር ያላቸዉን ግንኙነት ጨምሮ ደፈር ባለ አገላለጽ ("ሃፍረታቸዉ" ከማለት አያልፍም) ለሥነ ጽሁፉ ዉበት ይሰጠዋል። ይህ አገላለጽና ዘዬ በነ "ፍቅር እስከ መቃብር" ሊታሰብ የማይችል፤ ጊዜ አመጣሽ፤ ከነበ አሉ ግርማና ብርሃኑ ዘሪሁን የልብ ወለድ ሥነ ጽሁፍ ጀምሮ በስፋት የታየ መሆኑ ይስተዋላል።**

## ለመግቢያ ያህል

**አዳም ከሥነጽሁፍ ባሻገር በሌሎችም የሥነ ፈጠራ መስኮች ፍላጎትና እዉቀት እንዳለዉ ልብ ወለድ ስራዎቹ ጠቋሚ ናቸዉ። የሙዚቃ፤ የስእልና የመሳሰሉት ዘርፎችን ከፍተኛ ሚና በሚጫወቱ ገጸባህሪያቱ፤ ለምሳሌ መስኮት ገረሱን በሰአሊነት ስራዎቹ ዉስጥ ያካትታቸዋል። ሙዚቃንም በተመለከተ፤ እንደ "መረቅ" ባሉ በተለይ የቅርብ ስራዎቹ፤ በጣም "ምእራባዊ" ተብሎ ሊያሳማዉ በሚችል ደረጃ የማይጠቅሳቸዉ የፈረንጅ ዘፈኖች የሉም ሊባል ይቻላል። ሃዲስ አለማየሁ ጉባኤ ቃና፤ መወድስ፤ 12 ሙሉ ቤት መዝሙር፤ ከቅኔ ድርና ማግ የተሰራ አእምሮ፤ ማህሌተ ገንቦ፤ ወዘተ...እያሉ በ "ፍቅርና መቃብር" ከግእዝ መሰረታችን እየቀዱ የሚያፈሱትን፤ አዳም ረታ ባህር ማዶ ተሻግሮ የ ዱክ ኤሊንግተን ብሉ ቤሪ ሂልን (እቴሙቴ የሎሚ ሽታ -ለነገሩ ኤሊንግተን ሳይሆን ፋትስ ዶሚኖ የተባለ ዘፋኝ የዘፈነዉን))፤ ዎዎዎዎ ሺ ኢዝ ኤ ሌዲንና የሬይ ቻርልስን ዘፈን (አለንጋና ምስር) የመሳሰሉ ዘፈኖች፤ ገጸ ባህሪያቱ እንዲያዜሙና እንዲያዳምጡ ያደረገበትን ይጋብዘናል። ሃሜቱ ግን የጊዜን እንደ ጎርፍ ካንድ ትዉልድ ወደ ሌላ መተላለፍ ግምት ዉስጥ ቢያስገባና ባህል ደግሞ በ አለም አቀፍ ደረጃም ጭምር ተወራራሽና አንዱ ካንዱ ተበዳዳሪ የመሆኑን ጠቃሚነት በማጤን ሚዛናዊ ፍርድ ላይ መድረስ ያስችላል።**

**አዳም ረታ እጹብ ድንቅ ጸሃፊ ነዉ ያልነዉን በ አነጻጽሮ ብናሳየዉ ነገሩን ግልጽ ሊያደርገዉ ይችላል። ከሃዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከ መቃብር" የተቀነጨቡትን እምቡጦች ለላንቲካ ያህል መጀመሪያ ለአነጻጽሮ እስቲ እንመልከታቸዉ።**

***እንደ ከፋ ቀን እህል እየተገበገቡለት" (እመት ጠጅቱ ለበዛብህ)**

***ያፈሰስኩት እንባ ሁሉ ለሞተ ዘመድ የሚበቃ ነዉ" (የበዛብህ እናት)።**

***"በሹም ትእዛዝ የተቀበሩ የበዛብህ ወላጆች"**

**"ማንኩሳን እንደ እናት አባቱ እንደተቀበረ ቆጥሮ ሁለተኛ ላያየዉ ወስኖ ወደ አዲስ አበባ አቀና" (በዛብህ)**

**"የተሰራበት ዘመን የተረሳ የእንጨት መሰላል ወደ ዲማ ቅኔ በት ፎቅ የሚያወጣ"**

**" አካላቸዉ ሲጋ ያልከበደዉ" (ደራሲዉ ያንዱን ባላባት ሰዉነት ሲገልጹ)**

**" በሁለት እጆች የማያነሱት የባላባት ልጅ ነዉ"።**

*******

አዳም ረታ በራሱ የሥነጽሁፍ ዘየ ልክ እንደ ሃዲስ አለማየሁ የሚያስደምሙ አገላለጾች ችሎታዉን ይመሰክራሉ። ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት።

"በብርጭቆ ቂጥ እርጥበት የተሰሩ ቀለበቶች ጨርቅ ያልለበሰዉን ጠረጴዛ ጠለል ሸፍነዉታል" (ከመረቅ)

" ሾርባ አገር ነዉ። ከከብት ግጦሽ ያመለጠ ጎመንና በግጦሹ የዳበረ የከብት ስጋ ያለበት" (ከመረቅ)

በደርግ ጊዜ የታሰሩትንና ያ ከፉ ተመክሮ ያስተሳሰራቸዉን፤ ፖለቲካዊ ቃልን በአናቱ በመድፋት ሲገልጻቸዉ

"ያገናኘን ከአንድ ብሄረሰብ መመንጨታችን ነዉ። ደርግ ያሰረዉ ትንግርተኛ ብሄረሰብ"(ከመረቅ)

የምስር ወጥ በእንጀራ የሙብላት አፍቃሪ ገጸባህሪን ሲገልጽ

"ሰለሄ መለሄ ጉሮሮ ማይነሄ ገብተህ ተነህነሄ" (ከአለንጋና ምስር)

ልጅ ገጸባህሪ የናቱን እንክብካቤ በከፉ ወቅት ሲገልጽ

"በደረቅ ሌሊት አብዮተኛና ጸረ አብዮተኛ ሲፈናከቱ፤ ከሰፈራችን እስከ ቄራ ባሩድ ሲንጣጣ ሞሳ ዙሪያየን እንደ ሃረግ ተጠቅላ፤ ፊቴን ጡቶቿ መሃል ደግፔ እናዉዛለሁ" (እቴሜቴ የሎሚ ሽታ)

## አዳም ረታና ቪቲንግሽታይን

ሌላዉ የአዳም ረታ ልዩ የአጻጻፍ ስልት አጠር መጠን ያሉ ሚስጢራቸዉን ለማወቅ ደግሞ ደጋግሞ ማንበብን የሚጠይቁ ፍልስፍናዊ አንቀጾች መጽሀፉ ዉስጥ የመጠቀም ችሎታዉ ነዉ። ይህ በተለይ የሚያየዉ በ "መረቅ" ዉስጥ ነዉ። ለምሳሌ ያህል ከዚህ በታች የሰፈረዉን አንቀጽ እንመልከት።

"ዉስጤ ያ አለ። ዉስጤ ያች አለች። ዉስጤ ሁሉ አለ። አምላኪዉም የሚመለከዉም። ልቤ ሆደ ሰፊ ነዉ። እንኳን ሰዉ፤ የየረርን የተራራ ሰሰንሰለት የሚያጋድም። ሙሉኩሌዉ እዚህች ዉስጤ ያለ ጠሪ ተሰብስቧል። ማን ጠራዉ?

ዉስጤ አለ ማለት "አዉቀዋለሁ" ማለት አይደለም። የሚገርመኝ ሁሉ ዉስጤ ተሰብስቦ አጫዉቶና አስቆ ሊያሳድረኝ የሚችል ንቃት ነጥሮ አለመዉጣቱ ነዉ።" (መረቅ ገጽ 422)

እንዲህ አይነት አጫጭር፤ ቀዳሚዉና ተከታዩ የማይገናኙ፤ የፍልስፍና አንቀጾችን በመጻፍ የሚታወቅ ነምሳዊ ፈላስፋ ሉድዊግ ቪቲንግሽታይን የሚባል ነበረ። Philosophical Investigations በተባለ መጽሃፉ ካሰፈራቸዉ በርካታ አንቀጾች መካከል አንዱን ቀጥለን እንይ።

" When one means something, it is oneself meaning; so one is oneself in motion. One is rushing ahead and so cannot also observe oneself rushing ahead. Indeed Not." (p. 456)

ከላይ እንዳልነዉ እነዚህ የ አዳም ረታ አንቀጾች ልክ እንደ ቪቲንግሽታይን የፍልስፍና አንቀጾች ደግመዉ ደጋግመዉ ሊያነቧቸዉ ይገባል፤፡ እንዲያም ሆኖ የተለያየ አንባቢ የተለያየ ትርጓሜ ሊሰጣቸዉ ይችላል። ባጠቃላይ ግን ለጥቂት ሰዉ ብቻ፤ አንዳንዴም ለደራሲዉ ብቻ ተገላጭ ምስጢር እንዳላቸዉ ይሆናሉ።

አዳም በተያያዥ የሥነጽሁፍና ፍልስፍና መጋጠሚያ መስመርን ደጋግሞ የሚፈትሽ ጽሃፊ ይመስላል። እምቅ የፍልስፍና ፍላጎትና ችሎታ እንዳለ አንዳንድ ገጸባህሪያቱን ተመስለዉ የሚቀርቡ ጽንሰ ሃሳቦች በብዛት አሉ። የፈጣሪን ጉዳይ አስመልክቶ አንድ ሁለት ቦታ ላይ ሃይማኖታዊ ትችትም ባይሆን ጥያቄ ያነሳል ። አንድ ቦታ ላይ "አመክንዮ እንዴት ቢንሰራፉ ነዉ የእግዜርን ግርማ የጋረደዉ"? ይላል። ሌላ ቦታ ላይ ደግሞ "መጽሃፉ እግዜር

የበቀል አምላክ ነዉ ይላል" ይላል።

እንግዲህ ወደተነሳንበትና የትንተናችንም አላማ ወደሆነበት አቢይ ጉዳይ ማለፋችን ነዉ። እስካሁን ያቀረብናቸዉ፤ ዘዉ ብለን ወደ ጉዳያችን ከመግባታችን በፊት ልብ ወለድ ደራሲ አዳም ረታን ሊያስተዋዉቁ ይችላሉ ብለን ባሰብናቸዉ የመግቢያ ሃሳቦች ላይ ነዉ።

አንድ ደራሲና ከያኒ [ከማንኛዉም ሞያ በተለይና ከጋዜጠኝነት በስተቀር] ነገሮችን ከወገናዊነት በጸዳ መልኩ ያለ አድሎ በተሰማራበት ሙያ ሊያንጸባርቅ ይገባል። ይህ ሲሆን ግን እዉነትንና ፍትህን መሻት ወገናዊነት አያሰኝም። እዉነትና ፍትህ እንዲሰፍኑ የሰዉ ልጅ ዝንተ አለማዊ ጥረት ስለሆነ ከያንያን ይህን ጥረት ማጎልበት የሚጠበቅባቸዉ የሙያ ግዴታ ነዉ። ከከያንያን መሃከል አብዛኞቹ ግራ ቀመስ ፖለቲካንና የትግል መስኮችን ደጋፊ የሚሆኑት እዉነትንና ፍትህን የመሻትና የብዙሃንን ፍላጎት በማንጸባረቅ ነዉ። አዳም ረታስ?

## አዳም ረታና የአብዮታዊዉ ዘመን

አብዮታዊዉ ዘመን በተለያዩ ጸሃፍት በታሪክነቱ በወቅቱ ተወናዉያን በነበሩት ባለታሪኮች ዙሪያ (ስለ ደርግ፤ ስለ ኢህአፓ፤ ስለ ህወሃት፤ ስለ ሜኢሶን፤ ወዘተ) እየተዘገበ ይገኛል። ይህን ተከትሎ ደግሞ በታሪካዊ ልብ ወለድ መልክ ይህዉ ታሪክ ሲዘገብ እናያለን። በዚህ የሥነጽሁፍ ዘግ የቀንጂት ብርሃንን "ምርኮኛ" (ስለ ኢህአፓ)ና የሃብታሙ አለባቸዉን "የሱፍ አበባ" (ስለ ኢህአፓ)ና "የቄሳር እንባ" (ስለ ደርግ) በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል። በልብ ወለድ መልክ ደግሞ ከአዳም ረታ ስራዎች በዋነኛነት "መረቅ" ቀጥሎ በጥቂቱም ቢሆን "እቴ እሜቴ የሎሚ ሽታ" ገጸባህሪያን በማላበስ ዘመኑን ይቃኙታል።

አዳም ከላይ እንዳልነዉ ከያንያን ወገንተኛ ሳይሆኑ "ከሩቅ" በሃቅ ይተቹ ና ይተርኩ የሚለዉን መርህ ይከተልና መሰረታዊ ድክመቱ ግን በግላጭ ይወጣል። ይህም ድክመት የዚያን አብዮታዊ ትዉልድ፤ በተለይም የኢህአፓን ወጣት አባላት <u>ቅን ምኞትና ፍላጎት፤ ይህን ቅን ራእይም ለማሳካት ለመክፈል የደፈሩትንና የከፈሉትን መስዋእትነት</u> ብዙ ቦታ አይሰጠዉም። አዳም ረታ በመጽሃፍቱ የሚጠየፋቸዉንና የህብረተሰቡ ነዉር ናቸዉ የሚላቸዉን ጎጂ ባህሎችና ስርአቶች ለመታገልና ለመለወጥ እንደሞከሩ አይዘከርላቸዉም። "መረቅ" ላይ ገጽ 467 ማከዳ የተባለች ወጣት ልጅ በማስገደድ የተደፈረችበትን፤ በአቃጣሪዎች ወጣቷ ገላዋን የምትሸጥበት የገለማ ስርአት እንዲወገድ እስከ ህይወት የከፈሉ ታጋዮችን በችሮታ መዘከር ይነስ?

የአብዮታዊዉን ትዉልድ ስህተት ማንሳት፤ መተረክ ተፈላጊ ነዉ፡፡ አንዳንዶች በዚህ ትግል ያለፉት "ምን ተብሎ ስህተት ተነስቶ" የሚሉትም ከድንቁርና በመነጨ ትእቢት ጭምር ነዉ። በተያያዥ ግን በጎ አላማዉንና ለዚያ አላማ በቆራጥነት የተደረገዉን ዉሳኔ አብሮ ከትችት ጋር አለማየት፤ አንዳንዶቹ በጥላቻ ታዉረዉ ሌሎቹ በድንቁርና የሚሰሩትን ስህተት አዳም ሊያርመዉ ይገባል።

እንዲያዉም አንዳንድ ተቺዎች አዳም ከዚህም አልፎ በመጻህፍቱ አፍቅሮተ ደርግ (በጅምላ) አልፎ አልፎ ያንጸባርቃል ቢሉ የተከላካይ ዋቢ ለመጥራት ያስቸግር ይሆናል። ለማንኛዉም እስኪ ያሉንን መረጃዎች ከመጻህፍቱ እያጣቀስን ከዚህ በታች እንመልከት። ማስረጃዎች ስለሆኑ ሰፋ አድርገን ስለምንጠቅሳቸዉ አንባቢ ትእግስቱ እንዲኖረዉ እናሳስባለን።

## ትችቶቹ

በዋነኛነት የምንጠቅሳቸዉ ሁለት የአዳም ረታን መጻህፍት ነዉ። በመጀመሪያ "እቴ እሜት የሎሚ ሽታ" (2001)ን እንጠቅስና በተከታዮቹ ገጾች ደግሞ ወደ "መረቅ" (2007) እንሻገራለን። አንድ ቦታ ብቻ አለንጋና ምስር (2001) ላይ ደራሲዉ አብዮታዊዉን ትዉልድ በአዎንታዊ መልክ ገጸባህሪዉ በተሳተፈበት ሰላማዊ ሰልፍ የተካሄደዉን ድርጊት እናክላለን። አንባቢን በገጸባህሪያቱ ስምና መቼት አናሰለችም። ጥቅሱንና የተገኘበትን ገጽ ብቻ እናሰፍርና ትችታችንን ወደ መጨረሻ እናደርጋለን። አስፈላጊ ሲሆን ብቻ በየጥቅሱ ትንሽ መረጃ እናክላለን።

**

"ቤቴን እያፈረሱ ያልገባኝ መስሏቸዉ አፍጥጠዉ "ቤቴን እንየዉ" ብለዉ ይመጡና ስለ ዴሞክራሲ ጥሩነት፤ ስለመንግስቱ ሃይለማርያም መጥፎነት ያወሩኛል። ቤቴን እያፈረሱ፤ ንጉስ ያማሉ። አወናካሪዎች"። (ገጽ 120)

"ላም ሳር ሊግጥ፤ ዉሻ ቆሞ ሊሸና፤ እነዚህ ደግሞ እያበላሹ እንዲጠፉ የተሰሩ የታሪክ አንከሊሶች ናቸዉ። ታዲያ ፖለቲካ ያወሩኛል መጥተዉ። ደርግ ምንትሴ፤ መንግስቱ ቀባጥሴ። ቂልሽን ፈልጊ" (ገጽ 121)

ሰብለና ካሌብ ስለተባሉ ምናልባት በ ኢህአፓነት (በርግጠኝነት በጸረ ደርግ) ታስረዉ የነበሩ ገጸባህሪያት ፍቅረኞች

" እሱ (ካሌብ) ደግሞ ታሪክ ያዳክመዋል። "ያኔ የታሰርንበት ጊዜ፤ ምናምን" የሚባል ነገር ሰልችቶታል። "አታዉቀዉም እንዴ እሱን? ከፍተኛ አስር ቤት አብሮን ነበረ። ምናምን።" ከሚባል ነገር መራቅ ይወዳል። ስለተዋወቁበት የከፍተኛ 20 እስር ቤት ስለዚያም የ 3 ወር የስጋት ጊዜ አያወራም።

"እሱ ስለማንም (ስለ አሰረዉና ከመታሰሩ በፊት ስላገለገለዉ ድርጅት) ስለ ምንም (ስለ እስሩና አብሮት ስለ ሚመጣዉ የስነ ልቡና ጭንቀት) አያወራም"።

"ዛሬ ፍቅር መስጠት የማይችሉ፤ ዛሬን በመልካም በሚጥም መንገድ ማጠናቀቅ የከበዳቸዉ ጉድለታቸዉን ለሟሟላት ወደኋላ ስለሚሸሹ "የነበረ ወሬ" ይወዳሉ ብሎም አይደለም። ፍልስፍና የለዉም፡፤ በአጭሩ "ያኔ የታሰርን ጊዜ" ብሎ ትዝታ ማዉራት አይሻም።

ሰብለ እንግዲህ ያለፈ ታሪክን እያስታወሰች ዛሬ ካሌብን ቁም ነገረኛ ለማድረግ የምታደርገዉን ጥረት ደራሲዉ ዉሸተኛና አሰልቺ አድርጎ ገጸባህሪዋን ይስለዋል።

በሌላ በኩል አዳም "ከሩቅ" ሆኖ ከሚያቀርባቸዉ ትንተናዎች ስሜት የሚሰጡ (ትንሽ ቢያጋነዉም) የሚከተሉትን የመሳሰሉ ይገኛሉ።

"ትዝ ይልሃል።ፖለቲካ ገብተህ በነበረ ጊዜ ገና በልጅነትህ? አቀላጥፎ ተናጋሪ ነበርክ። ብሩህ ትመስል ነበር። ግን ምንም አታዉቅም። ዛሬ የተሻለ ታዉቃለህ፤ የተሻለ ይገባሃል፤ ግን ትንተባተባለህ። ብዙ ተፎካካሪ ሃሳቦች አእምሮህ ዉስጥ ስላሉ ትክክለኛዉን ለመምረጥ ጊዜ ስለሚወስድብህ ይሆናል።" (ገጽ 202)

በተመሳሳይ ስለወጣት ስነልቦና ደርግ ባንድ ወቅት "ወጣነት ለጸረ አብዮት ስራ ላይሰንስ አይደለም" ያለዉን አይነት አንድሞታ ያለዉ አባባሉን እንዲህ ያቀርባል።

"ወጣቶች በአብዛኛዉ የማያስቆጣ ያስቆጣቸዋል። ቶሎ ያኮርፋሉ። ሁሉን ነገር ያለ ቁጥጥር ያለ ጠባቂ ለመስራት ይፈልጋሉ። ለእዉቀት ሳይሆን ለድርጊት ይቸኩላሉ። ምክንያት ቢኖራቸዉም ባይኖራቸዉም አዛዉንት ይጠላሉ። ደማቸዉ ነጋ ጠባ ይፈላል። ይንተከተካል። ፍላሎት ስላለባቸዉ ባያዉቁም እናዉቃለን ይላሉ። ለአገር መጥቀም የሚጀምሩት እነዚህን የፍላሎት እንቅፋቶች ያለፉ ናቸዉ። ህ/ሰብን ለመጉዳ የሚጠቀሙበት ይኖራሉ። የትኞቹ ጎጅዎች እንደሆኑ መገመት አይገድም።" (ገጽ 284፤ ግርጌ ማስታወሻ 145)

ገጽ 208 ላይ ደግሞ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መሪ አይነት የነበረ ታስሮ የተፈታ ሪቮ የሚለዉ ዳዊት ገ/ኢየሱስ የተባለ ገጸባህሪ ቀለመወርቅ የተባለች ባለትዳርን አማጋጭና ጥልቀት የሌለዉ "የተናገረዉ ነገር መሬት የሚወድቅ" ከእጁ የሌኒንን መጽሃፍ የማይለይ አድርጎ ያቀርበዋል።

ስለተማረበት ት/ቤት በትዝታ እያስታወሰ አንዱ ገጸ ባህሪ ደግሞ የሚከተለዉን ይላል። ወጣቱን አብዮታዊ ትዉልድ የሚወርፍ ይመስላል።

"ጥልቀቱንና ስፋቱን ባልተረዱት ፖለቲካ ነፍሳቸዉ ከጠፋና ህልማቸዉ ከተዳፈነ አንዳንድ የእድሜ እኩያዎቼ ጋር አነጻጽረዉ ጉዞየ ብዙ ጀብዱ የሌለዉ ምስኪን እንደሆነ ሁሉ ሊነግሩኝ የሚፈልጉ አራዳ ነን ባዮች አሉ። ያልገባኝን አድርጌ አልዉቅም።" (ገጽ 234)

የ"እቴሜቴ የሎሚ ሽታን" ጥቅሶች ከመዝጋታችን በፊት አዳም ረታ ለትችታችን ዋቢ የመጨረሻ ማስረጃ ከዚህ መጽሃፍ እንደሚከተለዉ ያቀርብልናል።

"ፖለቲከኛ ለምን እንደሆኑ ፤እንዴት እንደሆኑ፤ ምን እንደሚያዉቁ ስጠይቃቸዉ የሚናገሩት ነገር ባዶ ሊሆን ምንም አይቀረዉ። ከዚህ አረፍተ ነገር ቀጥሎ እንዳለዉ ቦታ..." ይልና አዳም ረታ ከበድ ያለ ከገጽ መጀመሪያ መጨረሻ የሚደርስ ጥቁር መስመር ይሰራል። (ገጽ 234)

በግርጌ ማስታወሻ ደግሞ "ይህን የጨለማ ቦታ አንድ አርታኢ ወዳጄ "የብረት ዲሲፕሊን" በለዉ ብሎኛል" ብሎ ይሳለቃል።

ቀጥለን ደግሞ ከ "መረቅ" የምናገኛቸዉን እናቅርብ። "መረቅን" ከሌሎቹ መጽሃፍት የሚለየዉ ለፖለቲካ የሰጠዉ ሰፊ ቦታ መሆኑና ኢህአፓን በስም ባይወቅስም በልሳኑ በዴሞክራሲያ በሚያደርገዉ ስላቅ ነዉ። አዲስ አበባ ዉስጥ የሽሮ ሜዳ አካባቢን መሰረት በማድረግ አብሮ አደግ የሰፈር ልጆች ወደተለያየ አቅጣጫ በአብዮቱ ወቅት ሲበታተኑ መጽሃፉ ያሳያል። የኢህአፓ አባል በነበረችዉ ተባረኪና ፖለቲካ በማይወደዉና በማይገባዉ የወንድ ጓደኛዋ አላዛር መካከል ያለዉን ዉጥረትና ሰቀቀን በጥሩ ሁኔታ ይተርካል። ስለተባረኪና ኢህአፓ ሲያወራም "እንደተባረኪ ያሉትን ብሩህ አእምሮ ያላቸዉን አስቀድማ መልምላ ቀጥላ ደደቦችን ስትመለምል ፕሮፓጋንዳ መስራቷ ነዉ - በትእቢትና በመምሰል የሚተሳሰሩበት አባሎች" (ገጽ. 475).

አልፎ አልፎም "አብዮቱንና መሪዉን እየተሳደቡ" እያለ የወገናዊነት ቀይ መስመሩን ይጥሳል።

የኢህአፓ አባል ተባረኪ እስር ቤት ጨርሳ፤ ከአላዛር ሴት ልጅ ወልዳ፤ ከአዲስ አበባ አዋሳ ኑሮ ቀይራ፤ እንደሷዉ የኢህ አፓ አባል የነበረና ታስሮ የተፈታ ፋሲል የሚባል ባል አግብታ (ፖለቲካ የማይወደዉ አላዛር ገና የ 66ቱ ፖለቲካ መሞቅ ሲጀምር ዘመዶቹ ወደ አዉሮጳ ልከዉታል -ቢኖርም አብረዉ መቀጠላቸዉ አጠራጣሪ ነበር)።

ተባረኪ እንዲህ ትላለች።

"አንድ ቀን ሙዚቃ እየሰማሁ አሱንም ተከትየ እያንጎራጎርኩ ጊዜዉ ደርሶ እራት ላደርስ ወዲያ ወዲህ ስል ፋሲል የተጠረዘ ነገር አምጥቶ ፊቴ ላይ ዘጭ አደረገ። ፈገግታዉም ልዩ ነበር። ወፍራም ፊቱ ላይ አንድ ትልቅ ቀዳዳ ተከፈተ።

"ምንድን ነዉ?" አልኩት።
"ለትዝታ። ልሳናችን"።
"የምን ልሳን?"
"እይዉ"።

እርጥብ እጄን በቀሚሴ ጠራርጌ ፋይሉን አነሳሁና ገለጥኩት።ደነገጥኩ።
"የት አገኘሀዉ?"

"ሽፈራዉ አዋሰኝ"።
ከሁለቱ በስተቀር ሁሉም እትሞች አሉ። ቃሉ ራሱ ደስ ይላል። ደሞክራሲያ።
የተጻፈበት ቀይ ገርዳፋ ቀለምና የቀለሙ ጥልቀት ልብ ይገባል። ፓምፍሌቶቹ በጥንቃቄ ተጠርዘዋል። የአተያየቡ ስልት በትዉስታ ናጠኝ።"

ከዚህ በኋላ አዳም ረታ ገጸባህሪያቱን ያሰናብትና "መረቅ" ከገጽ 306-314 እያለፈ እያለፈ የዴሞክራሲያ እትም ቅጽ 4 ቁጥር 9 የሚለዉን በሰፋት ይጠቅሳል። አላማዉ ግልጽ ይመስላል። ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ላለው ችግር ኢህ አፓ በብቸኝነት ተጠያቂ ለመሆኑ የጻፋቸዉ ጽሁፎች በኤግዚቢትነት ሊያገለግሉ ይችላሉ የሚል ይመስላል።

የጠቀሰዉን እንጥቀስ።

"ከሁሉም በላይ ፍጅቱን ለማስፋፋት ህዝቦችን እርሰበርሱ እያጣላ ነዉ። በጉርጉስም፤ በጋራ ሙለታና በሃብሮ አዉራጃዎች ህዝባዊ ጦር ብሎ ያሰለፈዉ በፊት ኦሮሞዎችን ይበዘብዙ የነበሩትን ነፍጠኞች ነዉ" ገጽ 306

"የኢትዮጵያ ታሪክ ሂደቱ የገፋበት ጊዜ መቶ አመት እንኳን አንዳልሞላዉ...." ገጽ 308

"ኢምፔሪያሊስቶች ሆኑ ሚኒሊክ ከዚያም ዘዉዲቱም ሃይለስላሴ አንዴ በስምምነት አንዴ በጦር ሃይል እያሉ ቅኝ ግዛት ሲያማርጡ ሲያስፋፉ እንዲያም ሲል በአካባቢዉ ነዋሪ የሆኑ ህዝቦችን ህልዉና ተገንዝበዉ..." ገጽ 312

*የሶማሌ ህዝቦች ሳያዉቁና ሳይፈቅዱ በምኒልክና በኢምፔርያሊስቶች ደባ በኢትዮጵያ ግዛት ስር ዉለዋል። ይህን እብሪት በመቃወም ሶማሌዎች በተደጋጋሚ እርምጃዎችን ወስደዋል" (ገጽ 314)

**

አዳም ረታ ዴሞክራሲያን እየጠቀሰ (ለዚያዉም እዉነተኛ የዴሞክራሲያ ቅጽ ከሆነ) አስተዛዛቢ ነዉ። የመጨረሻ የወገናዊነት ማስረጃችንም ጭምር ነዉ።

ለጊዜዉ ለክርክር ሲባል እዉነተኛ የዴሞክራሲያዊ ቅጽ ነው የተጠቀሰው እንበል። አላማዉን መገመት እንችላለን። አንድም እነ ተባራኪና ፋሲልን በተባባሪም የኢህአፓ አባላትን ሁሉ "ይህዉ የታሰራቹሁበትና የደከማችሁበት ትግል ለዚህ ሃገር ክዳት አላማ ነበር " ለማለት፤ አያይዞም "ዛሬ አገራችን ለደረሰባት የፖለቲካ ቀዉስ ምንጩ ኢህ አፓ ነው" ለማለት ይመስላል።

ቅጽ 4 ቁጥር 9 ዴሞ እዉነተኛ እትም እንኳን ቢሆን፤ ኢህአፓ ቅጽ 1፤ ቅጽ 2፤ ቅጽ 3 ወዘተ ዴሞ እትሞች ማዉጣቱና በነዚህም የሃገሪቱን በዚያ ወቅት የነበሩ ቁልፍ ጥያቄዎች እየተነተነ፤ አቅጣጫ እያሳየ፤ ወጣቱን፤ አርሶ አደሩን፤ ሴቶችንና ሰራተኞችን በምልአት አሳትፏል። ካነሳቸዉም ቋሚ ጥያቄዎች እስካሁን መልስ ያላገኙት የህዝባዊ መንግስት መመስረት ጉዳይ፤የአርሶ አደሩ የመሬት ባለቤትነት ጉዳይና መሬት ላራሹ፤ የብሄሮች እዉነተኛ ሙብትና የኤርትራ ጥያቄ በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ የመፈታቱ አስፈላጊነት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ/ናቸዉ።

ዴሞ ቅጽ 4፤ ቁጥር 9ን ፈልጎ አስፈላልጎ የጠቀሰ ደራሲ እዉነተኛ ቅጽ ቢሆን እንኳን "በሌላ በኩል ግን ኢህአፓ ለዴሞክራሲያዉ ህዝባዊ ስልጣንና ኢኮኖሚ አጋዥ የሆኑ የዴሞ እትሞችም ነበሩት" በሚል ማካካስ "ከሩቅ " ተመልካች ደራሲ የሚጠበቅ አልነበረንም?

ገጸባህሪያት ህይወት የላቸዉም። የደራሲዉ ፍጡራን ናቸዉ። ደራሲዉም ልብ ወለድ ድርሰት በመጻፍ ሽፋን የሚያምንበትን ወገንታዊ ፖለቲካ ገጸባህሪያቱን እያናገረ ከሃላፊነት ሊሸሽ አይችልም። አዳም ረታ በተለይ ኢትዮጵያ ዉስጥ ታዋቂ እየሆነ የመጣ፤ተነባቢነቱ እየሰፋ የሄደ ደራሲ ስለሆነ፤ ይህም ሃላፊነት ያለበት ሚና ነዉ። በተለይ የኢትዮጵያን አብዮት የማያዉቀዉን አዲስ ትዉልድ በተሳሳተና ሚዛናዊ ባልሆነ መረጃ መበከል ሃላፊነት የጎደለዉ ተግባር ነዉ።

አዳም ረታ ይህንን ሂስ በገንቢነቱ መልክ ተመልክቶ በወደፊት ድርሰቶቹ ማስተካከያ ያደርጋል ብለን እናምናለን።

በሌላ በኩል አለንጋና ምስር መጨረሻዎቹ ገጾች ላይ ላይ ፍሬዉ የተባለ የ 6 ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ገጸ ባህሪ፤ ለሰላማዊ ሰልፍ በ 66 ኢ.ም. ሲፈራና ሲቸር ወጥቶ ሰላማዊ ሰልፉ በሚያስለቅስ ጋዝና በተኩስ ሲበተን ከፖሊስ ለማምለጥ ስለተጠጋባቸዉ የደሃ ቤት ጥሩ ታሪክ አቅርቧል። ሴትዮዋ ጠላና አረቂ በመሸጥ የሚተዳደሩ ናቸዉ። ጥቂት ደምበኞቻቸዉን እያስተናገዱ እያለ ነዉጡን ሰምተዉ ሲወጡ፤ ፍሬዉ ተባራሪ፤ፖሊስ አባራሪ ይሆንና ሴትዮዋ በመካከላቸዉ ገብተዉ ሊገላግሉ ይሞክራሉ። ራሱ በመድማት ላይ የነበረዉ ፖሊስ፤ ሴትዮዋን ወደጎን ገፍቶ ፍሬዉን ባልተወለደ አንጀቱ ሰባብሮ ይደበድበዋል። ቤት አስገብተዉት ወደ ማምሻዉ ላይ ሽማግሌ ጡረተኛ ወጌሻ ከሌላ ሰፈር ተፈልጎለት፤ አሽተዉት፤ ቤት ያፈራዉን አብልተዉና አጠጥተዉት ወደ 6 ኪሎዉ ሲነጋ ይሸኙታል። የደሃ ፍቅርና ድጋፍ።

አዳም እንዲህ ባለ ሁኔታ እየተሰቃየ የሚኖረዉን ኢትዮጵያዊ ኑሮ፤ የእለት ጉርሷን ለማግኘት የምትባዝነዉን፤ ባንጻሩ ደግሞ በንቅዘትና በጥጋብ የሚኖረዉን፤ ሃሳቡን በነጻ ስለገለጸ በእስር የሚማቅቀዉን የመሳሰለ በገጸ ባህሪያት መልክ በይበልጥ ቢያቀርብና መጽሃፉቶቹን የሚያስደምመዉን የአልጋና የሴትና ወንድ ግንኙነት ትረካን ቀነስ ቢያደርግ ምናልባት በይበልጥ የደራሲነት ህዝባዊ ወገንተኝነቱን ማረጋገጥ ይችላል ብለን እናምናለን።

ሰኔ 2008 (June 2016)